



# «መልእክትሽ ደርሶናል!»



[ለብርቱካን ሚደቅሳ]

እምቡጥ ለጋ ሕይወት፣
የተሰፋ ምልክት፤
ብርቱካን መሳይዋ፣
የአድማስ ፀሐይዋ፣
የእናት አርበኞቿን ፈለግ ተከታይዋ፤
ሩህሩህ ለወገኗ ለጠላቷ ብርቱ፣
የእማማ «ባፈና» የእቴጌ ጣይቱ ...
ምትክ ወጣቲቱ።

... የአምባገነን ብረት ወህኒ ሳይበግረው፣
«መንፈስሽ» ደርሶናል የሚንቦገቦገው፤
ኃያል ነው ሙቀቱ፣
ለሕዝባዊነቱ !
ቃጠሎ ነው ብርቱ፣
ንዳድ ለጠላቱ !

እውነት ስትጠራ፣
እንደ ንጋት ጮራ፤
የፍርድ ቀን ሲደርስ፣
ጨቋኝ ሲገረሰስ፤
ፍትህ፥ ሠላም ... ሰፍኖ፣
ቃልሽ እውን ሆኖ፤
ኢትዮጵያችን ድና፣
ለማየት ያብቃና !!!

እምቡጥ ለጋ ሕይወት፣
የተሰፋ ምልክት፤
ብርቱካን መሳይዋ፣
የጠዋት ጮራዋ፤
እሰይ ተባረኪ ! የሁላችን አርማ፣
የጭንቅ ዘመን ልጅ የኢትዮጵያ የእማማ፤
ደግሞ እንደ ደራርቱ ባንዲራዋን ለብሰሽ፣
ለዓለም ለማሳየት ... ለዚያች ዕለት ያብቃሽ !!!

ጌታቸው አበራ
2006